# ምድብ ሁለት (ከ1ኛ — 3ኛ) ክፍል

## 21 ኛ ሳምንት

### ክርስቶስ በቤተመቅደስ

**ዓላማ**

- ❖ ቤተክርስቲያን የጸሎት ቤት መሆኗን መማር፡፡

**ምንባባት**

- ❖ ማቴ 21, ዮሐ 2

**መግቢያ**

- ❖ በዛሬው ትምህርታችን በቤተመቅደስ ሲፈጸም የማይገባ ሲሠሩ ያያቸውን ጌታ ምን እንዳደረገ እንማራለን፡፡
- ❖ በቤተመቅደስ ልንጠብቀው ስለሚገባን ሥርዓትም አብረን እናያለን፡፡

**የክለሳ ጥያቄዎች**

1. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እውሩን እንዴት አዳነው?
2. ለምን ታወረ?
3. ከዳነስ አመነ? ወይስ…..

**ትምህርቱ**

- ❖ አንድ ቀን ጌታችን በኢየሩሳሌም ወደ ነበረው ቤተመቅደስ ሲሄድ÷ሕዝቡ በቤተመቅደስ ከብት፣ በግ፣ ርግብ ሲሸጡና ገንዘብ ሲለውጡ አገኛቸው፡፡
- ❖ ልጆች ቤተመቅደስ ምንድነው? …. ጌታችን የተቆጣው ቤተመቅደስ ቅዱስ ቦታ ስለሆነና የገበያ ሥፍራ ስላልነበረ ነው፡፡ በዚህም ምክንያትም የእግዚአብሔርን ቤት ያበላሹትንና ሸቀጣቸውንም ከቤተመቅደስ አወጣ፡፡
- ❖ ***"ቤቴ የጸሎት ትባላች እናንተ ግን የወንበዶች ዋሻ አደረጋችኋት"*** አላቸው፡፡
- ❖ ሻጮችና ለዋጮችም ከቤተመቅደሱ ወጡ፡፡
- ❖ ቤተክርስቲያንም የእግዚአብሔር ማደሪያ ቤተ መቅደስ ነውና የጸሎት ቤት ናት፡፡
- ❖ ወደ ቤተክርስቲያን ስንመጣም የመስቀሉን ምልክት ማሠብና መጸለይ አለብን፡፡
- ❖ የመስቀል ምልክት እንዴት እንደምንሠራ ታውቃላችሁ? ስለማማተብ የተማራችሁትን ትምህርት አስታውሱ፡፡
- ❖ ወደ ቤተክርስቲያን ስንመጣ የራሳችንንና የልብሳችንን ንጽህና ጠብቀን መሆን አለበት፡፡
- ❖ ወደ ቤተ መቅደስ ስንገባም ጫማችንን እናወልቃለን፡፡
- ❖ የሌሎችን ጸሎት ሳንረብሽም መማርና መጸለይ አለብን፡፡ ይሄን ስንጠብቅም ጌታችን በእኛ ይደሰታል፡፡

**ጥያቄ**

1. ጌታችን ወደ መቅደስ ሲመጣ ምን አየ?
2. ጌታችን *'ቤቴ'* ምን ማድረጊያ ነው አለ?
3. በቤተክርስቲያን ምን ማድረግ አለብን?
4. በቤተክርስቲያን ለምን እናማትባለን?

**ምኩራብ**

- ❖ ምኩራብ ማለት ምን ማለት ነው? የጸሎት ቦታ ማለት ነው፣
- ❖ ከመቅደስ በምን ይለያል? ጸሎትና መጽሐፍ ማንበብ ብቻ ሲሆን እንደ ቤተመቅደስ ታቦት አልነበረውም፡፡
- ❖ የት ተጀመረ? አይሁድ በስደት እያሉ የጀመሩት ነው፡፡
- ❖ ይህ ሳምንት ለምን ምኩራብ ተባለ? ጌታችን በአይሁድ ምኩራቦች እየገባ ያስተምር እንደነበር ለማስታወስ፡፡
- ❖ በየትኛው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ላይ የጌታችን ታሪክ ይገኛል? ዮሐ.2÷12, ማቴ 4÷23

**መዝሙር**

ቤቴ ቤተክርስቲያን ናት (2)

የጸሎት ቤት ናት

**ይቆየን፡፡**